የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፵፩
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፱ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠ

18th Year No. 41
ADDIS ABABA 6th July, 2012


ማውጫ

**አዋጅ ቁጥር ፯፻፵፰/፪ሺ፬ ዓ.ም**


በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በህንድ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ …… **ገጽ ፮ሺ፫፻፷**


**CONTENTS**

**Proclamation No.748/2012**


Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of India for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation. ... Page 6360


## አዋጅ ቁጥር ፯፻፵፰/፪ሺ፬

## በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በህንድ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በህንድ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችል ስምምነት እ.አ.አ. ሜይ ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፩ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፬ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION No. 748/2012.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE REPUBLIC OF INDIA FOR THE AVOIDANCE OF DOUBLE TAXATION AND THE PREVENTION OF FISCAL EVASION WITH RESPECT TO TAXES ON INCOME

WHEREAS, Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of India for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income was signed on 25th May 2011, in Addis Ababa;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 21st day of June 2012;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በህንድ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፵፰/፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በህንድ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል እ.አ.አ ሜይ ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፩ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመው በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችለው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፫. **የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

፬. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፱ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም**

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of India for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation No.748/2012".

**2. Ratification of the Agreement**

The Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of India for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income signed on 25th May 2011is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to implement the Agreement in cooperation with the concerned government organs.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 6th day of July, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**